በፌደራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 14 መሠረት የቀረበ ማብራሪያ

መግቢያ

የኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 332/2007 መሠረት የተቋቋመ የመንግስት መሥሪያ ቤት ነው፡፡ በአዋጅ እና በደንቡ ቦርዱ የተለያዩ ሥልጣን እና ተግባራት የተሰጡት ሲሆን ከእነዚህም መካከል ለሕዝብ አገልግሎት ለሚሰጡ የሒሳብ እና የኦዲት ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ መስጠት እና ለሒሳብ ሙያ ማኅበራት ዕውቅና/አክሪዲቴሽን መስጠት ይገኝበታል፡፡ ይህንን ተግባሩን በአግባቡ ለመወጣት ያስችለው ዘንድ ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ መመሪያ በማውጣት (መመሪያ ቁጥር 805/2013) አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

ይሁን እንጂ በአገራችን የካፒታል ገበያ መቋቋምን ተከትሎ የሕዝብ ጥቅም ላለባቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት የኦዲት አገልግሎት ለሚሰጥ ፐብሊክ ኦዲተር ፍቃድ መስጠት የሚያስችል መስፈርት መወሰን በማስፈለጉ፣ እንዲሁም በሥራ ላይ ባለው መመሪያ አፈጻጸም ወቅት የታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት እና በመመሪያው ውስጥ ያልተሸፈኑ አዲስ ጉዳዮችን በማካተት ወቅቱን ያማከለ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ በሥራ ላይ የሚገኘውን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት መንግሥታዊ አሰራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን እንዳለበት እና ማንኛውም የመንግሥት ባለሥልጣን ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ እንደሚሆን የተመለከተ በመሆኑ የአስተዳደር ተቋማት በሰዎች መብቶችና ጥቅሞች ላይ የሚያስከትሉትን ጣልቃ ገብነት በሕግ የሚመራና ለሕግ የሚገዛ መሆኑን ለማረጋገጥ ከወጡ የሕግ ማዕቀፎች ውስጥ የፌደራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ተጠቃሽ ነው፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 እና 14 መሰረት ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም መመሪያ በሚያወጣበት ጊዜ መመሪያው የወጣበት የሕግ መሰረት እና ዓላማ፣ በረቂቅ መመሪያው እና መጨረሻ ሆኖ በወጣው መመሪያ መካካል የይዘት ልዩነት ካለ የተደረጉትን ለውጦች ከነ ምክንያቶቹ የሚገልጽ ማስታወሻ እንዲሁም ረቂቅ መመሪያው ላይ የቀረቡ አስተያየቶች እና የተወሰዱ እርምጃዎች የያዘ ማብራሪያ

በማዘጋጀት ለፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ-ሕግ (ለፍትሕ ሚኒስቴር) መላክ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ (ቦርድ) በአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት ይህንን ማብራሪያ አዘጋጅቶ አቅርቧል፡፡

<u>ዓላማ</u>

መመሪያው ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ የቆየ ሲሆን መመሪያውን ማሻሻል ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያቶች በካፒታል ገበያ ላይ የሚሳተፉ ሪፖርት አቅራቢ አካላትን ጨምሮ የሕዝብ ጥቅም ላለባቸውን ሪፖርት አቅራቢ አካላት የኦዲት አገልግሎት ለሚሰጡ ባለሙያዎች (ፐብሊክ ኦዲተሮች) ቦርዱ በተለየ መሥፈርት ፈቃድ እንደሚሰጥ በአዋጅ ቁጥር 847/2006 የተደነገገ በመሆኑ ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ ያስችል ዘንድ የፈቃድ መስጪያ መስፈርቶችን ለመወሰን እንዲሁም በአፈፃፀም ወቅት በመመሪያው ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን በተመለከተ መፍትሔ ለማበጀት ነው፡፡

በተጨማሪም በመመሪያው መሠረት ፈቃድ የሚሰጣቸው ባለሙያዎች እና ድርጅቶች ጥራት ያለው እና ደረጃውን የጠበቀ ሙያዊ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል፣ ያለባቸውን ኃላፊነት በግልጽ ለማስቀመጥ እና እነዚህን ኃላፊነቶች በአግባቡ መወጣት ሳይችሉ ሲቀሩ የሚኖርባቸውን ተጠያቂነት ለመወሰን ነው፡፡

መመሪያው የወጣበት የሕግ መሠረት

በመሆኑም የኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 አንቀጽ 4(2)(ሀ) እና አንቀጽ 53(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት መመሪያ ቁጥር 805/2013'ን የሚያሻሽል "የሒሳብ እና የኦዲት ባለሙያዎች ፍቃድ አሰጣጥ እና የሒሳብ ሙያ ማኅበራት ምዝገባ መመሪያ ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር…………/2017" አዘጋጅቷል፡፡

በረቂቅ መመሪያው ዝግጅት ወቅት የተከናወኑ ተግባራት

በፌደራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 7 መሠረት የረቂቅ መመሪያውን ዝግጅት በሚመለከት ሰፊ ስርጭት ባለው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥቅምት 10 ቀን

2017 ዓ.ም በወጣው ዕትም እና የተቋሙን ድረ-ገጽ ጨምሮ በሌሎች ማኅበራዊ ሚዲያዎች ማስታወቂያ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 9 መሠረት በረቂቅ መመሪያው ላይ የሚመለከታቸው የአስተዳደር ተቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት አስተያየት እንዲሰጡ መላክ እንዳለበት የተደነገገ በመሆኑ ከአስተዳደር ተቋማት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ፣ የኢ.ፌ.ድ.ሪ. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር፣ የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት በፌደራል እና በክልል የሚገኙ የሒሳብ እና የኦዲት ሙያ ማኅበራት በረቂቅ መመሪያው ላይ አስተያየት እንዲሰጡ አስራ አምስት የሥራ ቀናት በመስጠት አስተያየት ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 10 መሠረት በረቂቅ መመሪያው ላይ የጽሁፍ አስተያየት መቀበያ ጊዜ ካበቃ በኋላ እና መመሪያው ከመጽደቁ በፊት ማንኛውም ሰው የሚሳተፍበት የውይይት መድረክ በገንዘብ ሚኒስቴር የስብሰባ አዳራሽ በማዘጋጀት ታኅሣሥ 14 ቀን 2017 ዓ.ም ግብዓት መሰብሰብ ተችሏል፡፡

በረቂቁ እና በመጨረሻው መመሪያ መካከል ያለ የይዘት ልዩነት

ለሚመለከታቸው አካላት በማስታወቂያ በተሰራጨው ረቂቅ እና የመጨረሻ ሆኖ በወጣው መመሪያ መካከል የይዘት ልዩነት የለም፡፡

በረቂቅ መመሪያው ላይ የተሰጡ አስተያየቶች እና የተወሰዱ ዕርምጃዎች

1. በአንቀጽ 2(4) ሥር "የሙያ ሥነ-ምግባር ደንብ" ለሚለው ሀረግ የተሰጠውን ትርጉም በሚመለከት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚወጣው የሥነ-ምግባር ደንብ በብዙ ባለሙያዎች እና ባለድርሻ አካላት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተመከረበት በመሆኑ መቀበል ወይም ማስማማትን ብቻ የሚጠይቁ በመሆኑ ቦርዱ የሚያወጣው የሚለው ቦርዱ የተቀበለው በሚል ቢተካ የሚል አስተያየት የቀረበ ሲሆን ቦርዱ በደንብ ቁጥር 332/2007 አንቀጽ 6(1) መሠረት ዓለም አቀፍ የሒሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን ወይም እርሱን የሚተካው አካል ከሚያወጣው የሥነ-ምግባር ደንብ ጋር የተጣጣመ የሒሣብ ባለሙያዎች እና ኦዲተሮች የሚመሩበት የሙያ ሥነ-ምግባር ደንብ ያወጣል የሚል ሥልጣን የተሰጠው

በመሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ የወጣን የሥነ-ምግባር ደንብ በቀጥታ የመቀበል እና ሥራ ላይ የማዋል ሥልጣን ያልተሰጠው በመሆኑ አስተያየቱን አልተቀበልነውም፡፡

2. በአንቀጽ 2(5) ሥር "አባል" ለሚለው ቃል የተሰጠውን ትርጉም በሚመለከት በአገራችን ውስጥ የዓለም አቀፍ የሒሣብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን ሙሉ አባል የሆነ አገር በቀል የሙያ ማኅበር የሌለ በመሆኑ በቦርዱ የሽግግር ግዜ ዕውቅና የተሰጠው ማኅበር የሚል ሃሳብ ቢካተትበት አሁን ያሉትን ማኅበራት በተወሰነ የጊዜ ገደብ ወደሚፈለገው ደረጃ እንዲመጡ ስለሚያስገድድ ትርጓሜው በዚህ መልኩ ማስተካከያ ቢደረግበት የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በአዋጁ እና በደንቡ ላይ የሽግግር ድንጋጌ የተቀመጠው ለባለሙያዎች እንጂ በአገር ውስጥ ላሉት የሒሳብ ሙያ ማኅበራት ባለመሆኑ፤ በዓለም አቀፍ የሒሳብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን ሙሉ አባል የሆነ በአገራችን ውስጥ የሚገኝ የተመሠከረላቸው የሒሳብ ባለሙያዎችን (ACCA) የሚያፈራ የውጪ አገር የሒሳብ ሙያ ማኅበር በመኖሩ፤ ድንጋጌው በዓለም አቀፍ የሒሳብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን እውቅና የተሰጠውን የሒሳብ ሙያ ማኅበር የሚያካትት በመሆኑ እና በቦርዱ አክሪዲቴሽን የተሚሰጣቸውን የሙያ ማኅበራት የሚያካትት በመሆኑ አስተያየቱን አልተቀበልነውም፡፡

3. በአንቀጽ 2(6) ሥር "ተገቢ የሆነ የኦዲት ድርጅት" ለሚለው ሀረግ የተሰጠውን ትርጉም በሚመለከት በተቋቋመበት አገር ሕግ መሠረት የኦዲት አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ፍቃድ የተሰጠው የውጭ አገር የኦዲት ድርጅት በዝርዝሩ ውስጥ እንዲካተት የተደረገ ሲሆን ነገር ግን የሙያ ፍቃድ ለግለሰብ እንጂ በቀጥታ ለድርጅት የማይሰጥ በመሆኑ በዚሁ አግባብ ማስተካከያ ቢደረግ የሚል አስተያየት የቀረበ ሲሆን አስተያየቱ ተቀባይነት አግኝቶ በድንጋገው ላይ ማስተካከያ ተደርጓል፡፡

4. በአንቀጽ 2(9) ሥር ብቁ እና ተገቢ ለሚለው ሀረግ የተሰጠውን ትረጉም በሚመለከት በድንጋጌው ሥር የተዘረዘሩት መገለጫዎች ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው፣ አሻሚ እና ላልተገባ የአሰራር ሁኔታ በር ሊከፍቱ ስለሚችሉ በድጋሜ ቢታዩ እንዲሁም በፊደል ተራ (ሐ) እና (ሰ) ላይ ማረጋገጫ የሚሰጡት ተቋማት ያልተገለጹ በመሆኑ መመዘኛዎቹ ግልጽ ቢደረጉ የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በፊደል ተራ (ሐ) ላይ አግባብነት ያለው አካል የሚል ሀረግ በመጨመር በድንጋጌው ላይ ማስተካከያ የተደረገ ሲሆን መመዘኛዎቹን በተመለከተ በዋነኛነት መመዘኛዎቹ ስለመሟላታቸው ማረጋገጫ የሚቀርበው/የሚሰጠው በእራሱ በባለሙያዉ ሲሆን በማንኛውም ጊዜ ባለሙያው ብቁ እና ተገቢ አለመሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ሲገኝ ተፈጻሚ የሚሆን ነው፤ ማስረጃውም ምን ሊሆን እንደሚችል

መመዘኛው በእራሱ አመላካች ስለሆነ (ለምሳሌ የፍርድ ቤት ውሳኔ/አባል የሆኑበት የሙያ ማኅበር ውሳኔ) አፈጻጸሙ አስቸጋሪ አይሆንም የሚል ድምዳሜ ላይ በመደረሱ የተሰጠውን አስተያየት አልተቀበልነውም፡፡

5. በአንቀጽ 2(9)(ረ) ሥር አመልካቹ የሙያ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል አካላዊ እና አዕምሮአዊ ብቃት ሊኖረው እንደሚገባ የተደነገገ ሲሆን አካላዊ የሚለው ቃል አግባብነቱ ቢታይ የሚል አስተያየት የተሰጠ በመሆኑ አካላዊ የሚለው ቃል ላልተገባ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል የሚል ውሳኔ ላይ በመደረሱ አስተያየቱ ተቀባይነት አግኝቶ ድንጋጌው ላይ ማስተካከያ ተደርጓል፡፡
6. በአንቀጽ 2(9)(ሸ) ሥር ብቁ እና ተገቢ ለሚለው ሀረግ በተሰጠው ትርጉም ሥር ብቁ እና በቂ ባለሙያዎች ያሉት የሚለውን መስፈርት አካትቶ የያዘ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ የሚይዘው ስንት ኦዲተሮችን እንደሆነ እና የሙያ ደረጃቸው ቢገለጽ የሚል አስተያየት የቀረበ ሲሆን በመመሪያው አንቀጽ 7(3)(ሸ) የተመሠከረለት ኦዲተር እንዲሁም በአንቀጽ 8(3)(ሸ) የፐብሊክ ኦዲተር ፍቃድ ለማግኘት የተቀመጠ ዝርዝር መስፈርት ያለ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ ስንት ኦዲተሮችን ያቀፈ መሆኑን እና የሙያ ደረጃቸው ምን እንደሆነ ትርጓሜ ሥር ማስቀመጡ አግባብ ስለማይሆን የተሰጠውን አስተያየት አልተቀበልነውም፡፡
7. በአንቀጽ 2(10) ሥር "የተከለከለ የኦዲት ሥራ ያልሆነ አገልግሎት" የሚለው ሐረግ ትርጉም የተሰጠው ሲሆን ክልከላ ከተደረገባቸው አገልግሎቶች ውስጥ አብዛኛዎቹ በኦዲት ድርጅቶች ቢሰጡ ተጠቃሚው የሚያተርፍባቸው እንጂ ጉዳት የማያስከትሉ እና ያለውን ውስን ባለሙያ በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል መሆኑን፤ ክልከላ ማድረግ ተገቢ ሆኖ ቢገኝ እንኳን በሁሉም ድርጅቶች ላይ ሳይሆን በካፒታል ገበያ ላይ ለሚሳተፉ ድርጅቶች በሚሰጥ አገልግሎት ላይ ብቻ ሊሆን ይገባል፤ ኦዲተሮች እንዳይሰሯቸው የተከለከሉ ተግባራት ከሆኑ በግልጽ ቢቀመጥ የሚል አስተያየት የቀረበ ሲሆን በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 9(6) ሥር እንደተቀመጠው ክልከላ የሚደረገው የኦዲት አገልግሎት በሚሰጥበት ዓመት እና በቀጣዩ ዓመት ባለው ወቅት ብቻ እንጂ አንድ የኦዲት ድርጅት በድንጋጌው ላይ የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች በአጠቃላይ እንዳይሰጥ የሚከለክል አይደለም፡፡ ይህም ባለሙያው እራሱ የሠራውን ሥራ እራሱ ኦዲት የሚያደርግበት ሁኔታ እንዳይፈጠር ለመከላከል እና ባለሙያው የሥነ-ምግባር ደንቡን ባከበረ መልኩ ገለልተኛ እና ከጥቅም ግጭት የፀዳ ሆኖ አገልግሎት መስጠት እንዲችል በመሆኑ፤ በተጨማሪም የኦዲት ሥራ ያልሆነ አገልግሎት የሚለው ሀሳብ ከዓለም አቀፍ የፋይናንስ ደረጃዎች የመነጨ ሲሆን

በደረጃው ላይ ለlisted company የኦዲት ሥራ ያልሆነ አገልግሎት በተሰጠበት ዓመት የኦዲት አገልግሎት መስጠት የተከለከለ በመሆኑ እና የሕዝብ ጥቅምን ለማስጠበቅ እንዲቻል በማሰብ በሌሎች የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት ላይም ተፈጻሚ መሆን ስለሚገባው አስተያየቱ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

8. በአንቀጽ 2(10) ሥር "የተከለከለ የኦዲት ሥራ ያልሆነ አገልግሎት" የሚለው ሥያሜ "የተፈቀዱ ሌሎች ከኦዲት ሥራ ውጪ የሆኑ አገልግሎቶች" በሚለው ቢተካ የሚል አስተያየት የቀረበ ሲሆን ሥያሜው "የኦዲት ሥራ ያልሆነ አገልግሎት" በሚል እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡
9. በአንቀጽ 2(11) ሥር ቢሮ ለሚለው ቃል ትርጉም የተሰጠ ሲሆን ቢሮ ለሚለው ቃል በአገሪቱ የንግድ ሕግ ላይ የተብራራ በመሆኑ በዚህ መመሪያ ውስጥ ማካተቱ ለምን አስፈለገ? አስፈላጊ አይደለም ቢወጣ የሚል አስተያየት የቀረበ ሲሆን የሒሳብ እና የኦዲት ባለሙያዎች አገልግሎት የሚሰጡበት ቢሮ ሊኖራቸው ስለሚገባ እና ቦርዱም የሙያ ሥራ ጥራት ማረጋገጫ ምርመራ ስለሚያከናወን ቢሮ የመያዝ ግዴታ ያለባቸው በመሆኑ እንዲሁም ባለሙያዎቹ ቢሮ ስለመያዛቸው የሚያቀርቡት የማስረጃ ዓይነት እና የቢሮ ኪራይ ውል የአገልግሎት ጊዜ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ የቀረበው አስተያየት ተቀባይነት አላገኘም፡፡
10. በአንቀጽ 3(2) ላይ መመሪያው በቦርዱ አክሪዲቴሽን ወይም ዕውቅና በተሰጣቸው የሒሣብ ሙያ ማኅበራት ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን የተደነገገ ሲሆን መመሪያው በኢትዮጵያ ውስጥ በሚንቀሳቀሱ የሒሳብ ሙያ ማኅበራት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል በሚል ቢስተካከል የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን ቦርዱ በአዋጁ ላይ የተሰጠው ሥልጣን ለሒሳብ ሙያ ማኅበራት እውቅና ወይም አክሬዲቴሽን መስጠት ሲሆን በቦርዱ ዕውቅና ወይም አክሬዲቴሽን ባልተሰጣቸው ወይም እንዲሰጣቸው ባልጠየቁት ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለተንቀሳቀሱ ብቻ መመሪያው ተፈጻሚ ሊሆንባቸው ስለማይችል አስተያየቱ ተቀባይነት አላገኘም።
11. በአንቀጽ 6 ሥር የሒሳብ ሥራ አገልግሎት ፍቃድ ለማግኘት መሟላት ካለባቸው መሥፈርቶች መካከል አመልካቹ የሒሳብ ሙያ ማኅበር አባል መሆን አለበት የሚል ሲሆን የሒሳብ ሙያ ማኅበር የሚለው የትኛውን ማኅበር እንደሆነ በግልፅ ቢቀመጥ ኤስ.ሲ.ኤ/ሲ.ፒ.ኤ ነው? እንዲሁም የሒሳብ ሥራ አገልግሎት ፍቃድ ለማግኘት በአካውንቲንግ ዲግሪ ያላቸው አመልካቾች ፍቃድ መከልከል ተገቢ ነው ወይ? ይህም

በኢትዮጵያ የተገኘ ዲግሪ ዕውቅና የሚነፍግ እና ከትምህርት ፖሊሲ ጋር የሚጋጭ አይሆንም ወይ? የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን የሒሳብ ሙያ ማኅበር የሚለው ሐረግ መመሪያውን ለማውጣት ሥልጣን በሚሰጠው የበላይ ሕግ አዋጅ ቁጥር 847/2006 ትርጉም የተሰጠው በመሆኑ እና በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 2 (11) ሥር በአዋጁ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላቶች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ የተጣቀሰ በመሆኑ፤ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 847/2006 እና በደንብ ቁጥር 332/2007 ላይ የሒሳብ እና የኦዲት ፍቃድ ለማግኘት የሒሳብ ሙያ ማኅበር አባል (የተመሠከረለት የሒሳብ ባለሙያ CPA) መሆን እንደ መነሻ መስፈርት የተቀመጠ በመሆኑ በመመሪያ ከዚህ ያነሰ መስፈርት ማስቀመጥ የሚፈቀድ ባለመሆኑ አስተያየቱ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

12. አንቀጽ 6(3)(ለ) ሥር የሒሳብ ሙያ ፍቃድ ለማግኘት የሒሣብ ሙያ ማኅበር አባል ከመሆኑ በፊት ወይም ከሆነ በኋላ ለ3 (ሦስት) ዓመታት በሒሣብ ሥራ ወይም በኦዲተርነት የሥራ ልምድ ያለው መሆን እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን የሒሳብ ሙያ ፍቃድ የሚሰጠው አመልካች አገልግሎት የሚሰጠው ለግሉ ዘርፍ/ንግድ ላይ ለተሠማራ ድርጅት በመሆኑ እና የሒሳብ አሰራሩ የተለየ በመሆኑ ከባለበጀት መሥሪያ ቤት ከሚቀርብ የሥራ ልምድ ይልቅ ከግል ዘርፍ የተገኘ የሥራ ልምድ ቅድሚያ ቢሰጠው የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን ከግል ዘርፍ ውጪ በሆኑ ድርጅቶች (በመንግስት እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች) ውስጥ ሲሰሩ የነበሩ አመልካቾች ተገቢ የሆነ የሥራ ልምድ የሚያገኙ በመሆኑ እና የዜጎችን የመሥራት መብት የሚያጣብብ በመሆኑ አስተያየቱ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

13. በአንቀጽ 6(3) (በ) ሥር አመልካቹ በቦርዱ ሲጠየቅ ለሙያ ሥራ ብቁ መሆኑን የሚያረጋግጥ የሕክምና ማስረጃ ማቅረብ እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን ድንጋጌው በአመልካቹ ላይ ጫና የሚፈጥር ሲሆን ብቁ ነው የሚባለውስ በምን መስፈርት ነው? የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን ድንጋጌው ለአላስፈላጊ አሰራር በር የሚከፍት በመሆኑ ከረቂቅ መመሪያው እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

14. በአንቀጽ 6(3) (ቀ) ሥር አመልካቹ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ማቅረብ እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን ከነዋሪነት መታወቂያ በተጨማሪ በአማራጭ መንጃ ፍቃድ ወይም ፓስፖርት ቢጠየቅ የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በደንብ ቁጥር 332/2007 አንቀጽ 17(2)(ለ) ሥር በኢትዮጵያ ውስጥ የሒሳብ ሥራ ለመሥራት ቋሚ ነዋሪ መሆን እንደ አንድ መስፈርት ተቀምጧል፡፡ ስለሆነም የአንድ አመልካች ነዋሪነት ሊረጋገጥ የሚችለው

አግባብ ባለው አካል የተሰጠ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም የመኖሪያ ፍቃድ በማቅረብ ነው፡፡ የተጠቀሱት ሰነዶች የአመልካቹን ማንነት ለማረጋግጥ የሚያግዙ እንጂ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ስለመሆኑ የሚያረጋግጡ ባለመሆናቸው አስተያየቱ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

15. በአንቀጽ 6(3) (ኀ እና ነ) አመልካቹ በዲሲፕሊን ያልተቀጣ ስለመሆኑ፣ መልካም ሥነ-ምግባር ያለው ስለመሆኑ እንዲሁም በወንጀል ያልተቀጣ ስለመሆኑ የጽሁፍ ማረጋገጫ እንዲያቀርብ የሚያስገድድ በመሆኑ ማረጋገጫ የሚሰጥ አካል የሌለ ስለሆነ አመልካቹ በእራሱ ቃል እንዲገባ ቢደረግ የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን የድንጋጌዎቹ ዓላማ አመልካቹ በእራሱ ማረጋገጫ እንዲሰጥባቸው ይደረጋል በሚል የተቀረጸ ሲሆን ገላጭ በሆነ መልኩ በአንቀጽ 2(9) ሥር እንዲካተቱ በማድረግ ማስተካከያ ተደርጓል፡፡

16. በአንቀጽ 6(6) እና 7(6) ሥር ከቦርዱ ፍቃድ የተሰጠው ባለሙያ በ2 ወራት ጊዜ ውስጥ የሙያ መድን ዋስትና፣ ንግድ ፍቃድ፣ ቢሮ እና ኦዲተር ከሆነ የኦዲት ቡድን ስለማደራጀቱ ማስረጃ እንዲቀርብ የሚደነግግ ሲሆን ዘላቂ የሆነ ቢሮ ለማግኘት እና አስፈላጊ ሁኔታዎችን ለማሟላት ረዘም ያለ ጊዜ ሊፈልግ ስለሚችል የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ወደ አራት ወር ከፍ ቢደረግ የሚል አስተያየት የቀረበ ሲሆን አመልካቹ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ማቅረብ ያለበት ፈቃድ ከማግኘቱ በፊት ሲሆን ነገር ግን ፍቃድ በተሰጠው የሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ እንዲያቀርብ ዕድል ተሰጥቶታል፤ ይህ ጊዜ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ለማቅረብ ከበቂ በላይ በመሆኑ እና በሥራ ላይ ባለው መመሪያ ላይ በዚሁ አግባብ (ሁለት ወር) የተቀመጠ እና በአፈጻጸም ላይም የተፈጠረ ችግር ባለመኖሩ አስተያየቱን አልተቀበልነውም፡፡

17. በአንቀጽ 7 ሥር የተመሠከረለት ኦዲተር ፍቃድ ለማግኘት መሟላት ካለባቸው መሥፈርቶች መካከል አመልካቹ የሒሳብ ሙያ ማኅበር ከሆነ በኋላ ተገቢ በሆነ ድርጅት ውስጥ ቢያንስ ለሁለት ዓመታት በኦዲተርነት የሠራ እና አንዱን ዓመት በኦዲት ማናጀርነት መሥራት እንዳለበት የሚደነግግ ሲሆን የኦዲት ሥራ ከፍተኛ ጥንቃቄ እና ልምድ የሚያስፈልገው በመሆኑ አመልካቹ ትምህርቱን የተማረው የኦዲት ሥራ እየሰራ ከሆነ አባል ከሆነ በኋላ የሦስት ዓመት ልምድ ቢጠየቅ፣ እንዲሁም ትምህርቱን የተማረው ከኦዲት ሥራ ውጪ ሆኖ ከሆነ አባል ከሆነ በኋላ የአራት ዓመታት ልምድ ቢጠየቅ እና ሁለቱ ዓመት በኦዲት ማናጀርነት እንዲሆን ቢደረግ የተሻለ ይሆናል ምክንያቱም አመልካቹ በሁለት ዓመት ውስጥ የኦዲት ፍቃድ ለማግኘት ይቅር እና በኦዲት

ማናጀርነት ማዕረግም ለማገልገል ብቁ ስለማይሆን የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በአገራች ውስጥ በቂ የሆነ ብቁ ባለሙያ (ሲ.ፒ.ኤ/የሒሳብ ሙያ ማኅበር አባል የሆነ) የሌለ በመሆኑ፤ ተገቢው እውቀት እና ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎች ብቻ ፍቃድ እንዲያገኙ ለማድረግ ያስችል ዘንድ በነባሩ መመሪያ ላይ ሲ.ፒ.ኤ. እንዲሆኑ ከሚያስገድደው መስፈርት በተጨማሪ ባለሙያዎች ተጨማሪ የኦዲት ትምህርቶችን እንዲወስዱ አዲስ መስፈርት እንዲካተት የተደረገ በመሆኑ ተጨማሪ ጥብቅ የሥራ ልምድ መስፈርት ማስቀመጥ ባለሙያዎች ወደ ሙያው እንዳይገቡ እና ሥራው በጥቂት ባለሙያዎች እጅ ብቻ እንዲወድቅ ያደርጋል፡፡ ይህም የአገልግሎት ጥራትን ጥያቄ ውስጥ የሚከት ይሆናል። በተጨማሪም የሌሎች አገራትን ልምድ ከግምት ውስጥ በማስገባት የተቀመጠ መሥፈርት በመሆኑ በተሻሻለው መስፈርት መሠረት የሚመዘኑ ባለሙያዎች አገልግሎት ለመስጠት ብቁ በመሆናቸው የተሰጠውን አስተያየት አልተቀበልነውም፡፡

18. በአማራ ክልል የኦዲት ሙያ ፍቃድ ለማውጣት ከ2-8 ዓመታት በውጭ ኦዲተርነት የሥራ ልምድ ሊኖረው እንደሚገባ የተገለጸ በመሆኑ ይህንን ተሞክሮ በመወሰድ መስፈርቱ ጥብቅ ቢደረግ የሚል አስተያየት የቀረበ ሲሆን በአማራ ክልል የሚጠየቀው የሥራ ልምድ መስፈርት የትምህርት ደረጃን መሠረት በማድረግ የተቀመጠ (ዲግሪ ላለው 8 ዓመት፣ ማስተርስ ላለው 4 እና ፒ.ኤች.ዲ ላለው 2 ዓመት) ሲሆን በቦርዱ የተቀመጠው መስፈርት Certified Public Accountant (CPA) መሆንን የሚጠይቅ በመሆኑ ሊነጻጸር ስለማይችል አስተያየቱ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

19. በአንቀጽ 7(3)(ለ) ሥር አባል ከሆነበት የሒሳብ ሙያ ማኅበር ሁሉንም የኦዲት እና ማረጋገጥ ትምህርቶች የወሰደ እና የተሰጠውን ፈተና ያለፈ በሚል ተደንግጓል፡፡ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የሒሳብ ሙያ ማኅበራት ትምህርት እና ፈተና በማይሰጡበት ሁኔታ እንደመስፈርት መቀመጡ ተገቢ አይደልም የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን ድንጋጌው ድንጋጌው ተፈጻሚ የሚሆነው ለተመሠከረላቸው የሒሳብ ባለሙያዎች ሲሆን አመልካቹ አባል (CPA) ከሆነበት የሒሳብ ሙያ ማኅበር የሚያቀርበው ማስረጃ እንጂ አገር ውስጥ ካሉት የሒሳብ ሙያ ማኅበራት የሚቀርብ ባለመሆኑ የተሰጠውን አስተያየት አልተቀበልነውም፡፡

20. በአንቀጽ 7(3)(መ) ሥር ከቦርዱ የተገኘ የሥራ ልምድ፣ በከፍተኛ የትምሕርት ተቋማት በመምህርነት በማገልገል የተገኘ የሥራ ልምድ እና በውስጥ ኦዲተርነት የሦስት ዓመታት

የሥራ ልምድ ያለው አመልካች ተገቢ በሆነ ድርጅት ውስጥ ለአንድ ዓመት በኦዲት ማናጀርነት ካገለገለ የተመሠከረለት የኦዲት ፍቃድ ማግኘት እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን የተጠቀሰው የሥራ ልምድ ከውጭ ኦዲት ሥራ ልምድ ጋር የማይሄድ በተለይም መምህርነት እና የውስጥ ኦዲት ለኦዲት ሥራ በቂ አይደሉም፤ በመሆኑም ለመምህር እና ለውስጥ ኦዲተር ለሦስት ዓመታት በውጪ የኦዲት ድርጅት ውስጥ የሠራ ተብሎ ቢገለጽ ወይም አጠቃላይ የሥራ ልምዳቸው አምስት ዓመት ሆኖ የሽግግር ሥልጠና ቢሰጣቸው የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን የኦዲት ፍቃድ ለማግኘት የሚያመለክቱ ሰዎች በቅድሚያ የዓለም አቀፍ የሒሳብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን አባል በሆነ የሒሳብ ሙያ ማኅበር/ኢንስቲትዩት የሚሰጠውን ትምህርት እና ፈተና በማለፍ የተመሠከረለት የሒሳብ ባለሙያ የሚል የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚጠበቅባቸው ሲሆን በተለይ የኦዲት ሙያ ላይ ለመሠማራት የሚፈልጉ ከሆነ ተጨማሪ የኦዲት ሥራ ልምድ በማቅረብ ከማኅበሩ የተሰጠ የሙያ ሥራ የምሥክር ወረቀት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ መመሪያ የተቀመጠው ተጨማሪ የስራ ልምድ የኦዲት ፍቃድ ለማግኘት በቂ በመሆኑ የተሰጠውን አስተያየት አልተቀበልነውም፡፡

21. በአንቀጽ 7(3) (ሸ) እና 8(3)(ሸ) ሥር የተመሠከረለት ኦዲተር ፍቃድ ለማግኘት አንድ የኦዲት ቡድን እንዲሁም ፐብሊክ ኦዲተር ከሆነ ሁለት የኦዲት ቡድን ሊኖረው ይገባል በሚል የተደነገገ ሲሆን በጉዳዩ ላይ የውጪ አገር ተሞክሮ ቢታይ፣ የኦዲት ቡድን በአስገዳጅ ሁኔታ ከመጠየቅ ይልቅ የደንበኛን ቁጥር መገደብ ቢቻል፣ በገበያ ውስጥ ያለውን የሰው ኃይል እጥረት ከግምት ቢገባ፣ አዲስ ጀማሪ ባለሙያዎችን የማያበረታታ እና ያሉትን ሊያፈናቅል የሚችል ነው፣ የኦዲት ቲም ምን ያህል ደንበኞች ማስተናገድ እናዳለበት የሚወሰነው በቲሙ ብቃት እና ኦዲት በሚደረገው ድርጅት ጥልቀት እና ስፋት በመሆኑ ለባለሙያው ቢተው፣ በኦዲት ቡድኑ ውስጥ የተመሠከረለት የሒሳብ ባለሙያ እንዲኖር መጠየቁ የአገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ ነው፣ ኪዚህ ይልቅ በአካውንቲንግ/በኦዲቲንግ ዲግሪ ያላቸው ሆነው ማኔጀሩ ስድስት ዓመት የሠራ እና ከዚህም ውስጥ ሁለቱ ዓመት በኃላፊነት ደረጃ ልምድ ያለው እንዲሁም ከፍተኛ ባለሙያው የአራት ዓመት የሥራ ልምድ እንዲኖረው ቢደረግ የተሻለ ይሆናል፣ ድንጋጌው ባለበት የሚቀጥል ከሆነ ከኦዲት የሥራ ልምድ በተጨማሪነት በአማራጭ የአካውንቲንግ የሥራ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ወደ ኦዲት ቡድኑ የሚቀላቀሉበት ሁኔታ ቢፈቀድ፣ የኦዲት ቡድኑ ውስጥ ፍቃድ የተሰጠው ባለሙያ የሚካተት መሆን

አለመሆኑ በግልጽ ቢቀመጥ የሚሉ አስተያየቶች የተሰጡ ሲሆን የኦዲት ቡድኑ ከቦርዱ ፍቃድ የተሰጠውን ባለሙያ ያካትታል ወይስ አያካትትም በሚል የተነሳውን ሀሳብ በተመለከተ አስተያየቱን በመውሰድ ከቦርዱ ፍቃድ ያላቸው ባለሙያዎች እንደ የኦዲት ቡድን ማናጀር እንዲቆጠሩ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

ከዚህ ውጭ የተሰጠው አስተያየት ግን ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ምክንያቱም የሕዝብ ጥቅምን ለማስጠበቅ እና የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል የኦዲት ድርጅቶች በተሟላ የሰው ሀብት ተደራጅተው አገልግሎት መስጠት እንደሚገባቸው የታመነበት በመሆኑ፤ ቦርዱ በኦዲተሮች ላይ ባከናወነው የኦዲት ሥራ የጥራት ማረጋገጫ በባለሙያዎቹ ላይ የሥራ ጥራት ክፍተት መኖሩ የተመላከተ ስለሆነ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ያግዝ ዘንድ የኦዲት ድርጅቶች በሥራቸው የኦዲት ቡድን እንዲኖራቸው ማድረጉ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም የተቀመጠው መስፈርት በተለይም ለተመሠከረለት ኦዲተር በቀላሉ ሊሟላ የሚችል ነው፡፡ ምክንያቱም ከቦርዱ ፍቃድ የተሰጠው ባለሙያ በግሉ የሚሰጥ ከሆነ በዘርፉ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ሁለት ሠራተኞችን ብቻ መቅጠር፤ ሁለት ሽሪኮች ያሉበት የሽርክና ማኅበር ከሆነ አንድ ሠራተኛ መቅጠር እንዲሁም ከሁለት ሽሪኮች በላይ የያዘ የሽርክና ማኅበር ከሆነ የኦዲት ቡድኑ በባለሙያዎቹ መካከል ሊቋቋም የሚችል ስለሆነ ተጨማሪ ሠራተኛ መቅጠር አይጠበቅባቸውም፡፡ ባለሙያው ፐብሊክ ኦዲተር ሆኖ በግሉ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ ሁለት የኦዲት ቡድን ሊኖረው የሚገባ ሲሆን በተመሳሳይ ከቦርዱ ፍቃድ የተሰጠው ባለሙያ የኦዲት ቡድኑ ማኔጀር መሆን ስለሚችል መቅጠር የሚጠበቅበት አንድ የተመሠከረለት የሒሳብ ባለሙያ እና አራት በዘርፉ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ሠራተኞችን ነው፡፡ ይህም ከተመሠከረለት ኦዲተር በተወሰነ ደረጃ መስፈርቱ እንዲጠብቅ የተደረገበት ምክንያት ድርጅቱ የኦዲት አገልግሎት የሚሰጠው ከፍተኛ የሕዝብ ጥቅም ላለባቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት ማለትም በካፒታል ገበያ ለሚሳተፍ ኩባንያ፣ ባንክ፣ ኢንሹራንስ፣ የመንግስት የልማት ድርጅት እና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት በመሆኑ ብቃት ባላቸው በቂ የሰው ኃብት ተደራጅቶ የኦዲት አገልግሎት እንዲሰጥ መደረጉ የአገልግሎት ጥራቱን ያስጠብቃል/ከፍ ያደርጋል በሚል ስለታመነ፡፡

22. በአንቀጽ 8 ሥር የፐብሊክ ኦዲተር ፍቃድ እንደሚሰጥ የተደነገገ ሲሆን ድንጋጌው የሌሎች አገራትን ተሞክሮ ከግምት ያላስገባ፣ ባለሙያዎችን የሚከፋፍል፣ ገበያው በሞኖፖሊ እንዲያዝ የሚያደርግ፣ አዲስ ገቢዎችን የማያበረታታ እና ISQM 1 and 2

ጋር የሚጻረር ሲሆን ማንኛውም የኦዲት አገልግሎት ISA እና ISQM ተከትሎ እስከተሰራ ድረስ የኦዲት ፍቃድ ክፍፍል ማድረጉ ተገቢነት የለውም፤ እንዲሁም የተመሠከረለት የሒሳብ ባለሙያዎችን የሚያፈራ ኢንስቲትዩት ባልተቋቋመበት ሁኔታ የተጠየቀው መስፈርት አስቸጋሪ አይሆንም ወይ? በተጨማሪም ACCA ላላቸው ባለሙያዎች ብቻ የሥራ ዕድል የሚከፍት በመሆኑ አግባብነቱ ቢታይ የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 847/2006 አንቀጽ 18 መሠረት የሕዝብ ጥቅም ላለባቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት የኦዲት አገልግሎት ለሚሰጥ ፐብሊክ ኦዲተር ፍቃድ መሰጠት እንዳለበት የሚደነግግ በመሆኑ እና የፐብሊክ ኦዲተር ፍቃድ ለማግኘት አመልካቹ የተመሠከረለት ኦዲተር ፍቃድ ሊኖረው እንደሚገባ የተደነገገ በመሆኑ ከዚህ የተለየ/ያነሰ መስፈርት ማስቀመጥ የማይቻል በመሆኑ አስተያየቱ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

23. በአንቀጽ 8(1) ላይ የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት እነማን እንደሆኑ በዝርዝር ቢገለጹ የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 847/2006 አንቀጽ 2(17) እና በሪፖርት አቅራቢ አካላት መለያ መስፈርት እና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 804/2013 ላይ ለሀረጉ ትርጉም የተሰጠው በመሆኑ አስተያየቱን አልተቀበልነውም፡፡
24. በአንቀጽ 8(3)(ሀ) ለአምስት ዓመታት የሙያ ማኅበር አባል መሆን የሚለው ስለሚበዛ እና አዲስ ገቢዎችንም ይገድባልኔሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን አንድ ባለሙያ ፐብሊክ ኦዲተር ለመሆን ከቦርዱ የተመሠከረለት ኦዲተር ፍቃድ ወስዶ ቢያንስ ለሦስት ዓመታት ያገለገለ መሆን ያለበት ሲሆን የተመሠከረለት ኦዲተር ፍቃድ ለማግኘት ደግሞ የሒሳብ ሙያ ማኅበር አባል ከሆነ በኋላ ለሁለት ዓመታት ተገቢ በሆነ ድርጅት ውስጥ የሥራ ልምድ ያለው መሆን ያለበት በመሆኑ የተቀመጠው አምስት ዓመት ይህን ሒደት ታሳቢ ያገረገ በመሆኑ አስተያየቱን አልተቀበልነውም፡፡
25. በአንቀጽ 8(3)(መ) ላይ በተናጠል ከሦስት ዓመታት በላይ አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተው በቅርብ ጊዜ የሽርክና ማኅበር ያቋቋሙ የኦዲት ድርጅቶች እንዴት ይታያሉ የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በተናጠልም ሆነ በሽርክና ከቦርዱ ፍቃድ ወስደው ለሦስት ዓመታት አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ባለሙያዎችን የፐብሊክ ኦዲተር ፍቃድ ማግኘት የሚችሉ መሆኑን በግልጽ በሚያሳይ መልኩ ድንጋጌው እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡
26. በአንቀጽ 8(3)(ረ) ቦርዱ ባከናወነው የኦዲት ሥራ ጥራት ማረጋገጫ ምርመራ ውጤት ወይም በክስ ሰሚ ችሎት ማስተካከያ እንዲያደርግ የተሰጠውን አስተያየት ወይም ትዕዛዝ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማስተካከል ቁርጠኛ ሆኖ እየሰራ ስለመሆኑ ከቦርዱ

ማስረጃ የተሰጠው የሚለውን በተመለከተ የጊዜ ገደብ ቢቀመጥለት የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን የጊዜ ገደብ የሚቀመጠው በምርመራው የተገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ ለባለሙያው በሚሰጠው አስተያየት ላይ የሚገለጽ በመሆኑ እና የሚሰጠው የጊዜ ገደብ በተገኘው ውጤት ዓይነት እና ክብደት ላይ የተመሰረተ እንጂ በመመሪያ ላይ የሚቀመጥ ባለመሆኑ አስተያየቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

27. በአንቀጽ 8(3)(ሰ) ላይ ተገቢ ቴክኖሎጂ እና ሶፍትዌሮችን በሥራ ላይ የማዋል ግዴታን በተመለከተ የኦዲት ሶፍትዌሮች መጠቀም ለባለሙያው የሚተው ቢሆን፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊተገበሩ አይችሉም፤ የውጭ ምንዛሪ፣ የቴክኒክ ድጋፍ እና የመሳሰሉትን ለመሟላት ቢያንስ ሁለት ዓመት ስለሚፈጅ የጊዜ ገደብ ቢቀመጥለት የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ እንዲሟላ ቢደረግ የሚለው አስተያየት ተቀባይነት አግኝቶ ድንጋጌው በዚሁ አግባብ እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡

28. በአንቀጽ 8(3)(ሸ) ላይ መልካም ሥነ-ምግባር ያለው ስለመሆኑ ከሚሰጥ አስተያየት ጋር በተያያዘ መስፈርቱ በባለሙያው እና በኦዲት ተደራጊ ተቋማት መካከል የሚኖር ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፤ የባለሙያው የሙያ ነጻነት እንዲገደብ ያደርጋል፤ ቦርዱ መርጦት አስተያየት የሚሰጥ ተቋም በአሰራር አለመግባባት የተፈጠረበት ከሆነ የሚሰጠው አስተያየት አግባብነት ላይኖረው ይችላል እንዲሁም በመቀራረብ ላይ የተመሠረተም ከሆነ በተመሳሳይ፣ ስለሆነም መስፈርቱ ለማረጋገጥ እና ለአሰራር ግልጽ ባለመሆኑ ቢወጣ የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን አስተያየቱ ተቀባይነት አግኝቶ ድንጋጌው ከረቂቅ መመሪያው እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

29. በአንቀጽ 8(3) የፐብሊክ ኦዲተር ፍቃድ ለማግኘት የሚፈልግ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 18 የተቀመጡት መስፈርቶች ማሟላት እንዳለበት የተጠቀሰ ሲሆን አንዱ መስፈርት በኢንስቲትዩቱ የሙያ ሥራ የምሥክር ወረቀት የተሰጠው መሆን እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን እስከአሁን ድረስ ኢንስቲትዩቱ ያልተቋቋመ በመሆኑ አዋጁ ላይ የተቀመጡትን ሁሉንም መሥፈርቶች አመልካች ማሟላት አለበት በሚል መቀመጡ ተገቢነት አይኖረውም የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን ምንም እንኳን ኢንስቲትዩቱ ያልተቋቋመ ቢሆንም የዓለም አቀፍ የሒሳብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን አባል በሆነ የሒሳብ ሙያ ማኅበራት ውስጥ አባል የሆኑ እና የሙያ የምሥክር ወረቀት የተሰጣቸው የተመሠከረላቸው የሒሳብ ባለሙያዎች በአገሪቱ ውስጥ ያሉ በመሆኑ እና ኢንስቲትቱ ሊያፈራ ከሚችለው ባለሙያዎች ጋር ከሙያ ብቃት አንጻር አቻ መሆናቸው

ስለሚታመን ከሌላ የሙያ ማኅበር የሙያ ምሥክር ወረቀት የተሰጣቸው ባለሙያዎች የሚስተናገዱ በመሆኑ፤ ነገር ግን እነዚህን ባለሙያዎች የማንቀበል ከሆነ በአገራችን ውስጥ የኦዲት ፍቃድ አውጥቶ ሥራ መስራት የሚችል አንድም ባለሙያ አይኖርም ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የተሰጠውን አስተያየት አልተቀበልነውም፡፡

30. በአንቀጽ 8(3)(ሀ) ሥር የፐብሊክ ኦዲተር ፍቃድ ለማግኘት ማንኛውም ባለሙያ ቢያንስ ከአምስት ላላነሱ ዓመታት ሳያቋርጥ የሒሳብ ሙያ ማኅበር አባል የሆነ እና ግዴታውን የተወጣ መሆን አለበት የሚል ሲሆን ፐብሊክ ኦዲተር ከሚጠበቅበት የአገልግሎት ግዝፈት እና ጥልቀት እንዲሁም ከሚያደርሰው ጉዳት አኳያ መስፈርቱ ከፍ ቢል የተለያዩ ጥቅሞች ስለሚኖሩት የፐብሊክ ኦዲተር ፍቃድ የሚሰጠው ቢያንስ ለሁለት ዓመታት የሽርክና ማኅበር መስርተው አገልግሎት ለሰጡ ባለሙያዎች መሆን አለበት የሚል መስፈርት ቢካተት ምክንያቱም አንዱ ሽሪክ የኦዲት ሥራው ላይ የሚሳተፍ ቢሆን ሌላኛው ሽሪክ ደግሞ የኦዲት ሥራ ጥራቱን የሚገመግም ይሆናል የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 847/2006 አንቀጽ 18 መሠረት የፐብሊክ ኦዲተር ፍቃድ ለአንድ ባለሙያ ብቻውን በመሆን ወይም ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር የሽርክና ማኅበር በማቋቋም አገልግሎት መስጠት የሚቻል መሆኑን በግልጽ የሚደነግግ በመሆኑ የተሰጠውን አስተያየት አልተቀበልነውም፡፡

31. በአንቀጽ 8(3)(ሸ) (በተሻሻለው መሠረት) ሥር ማንኛውም የፐብሊክ ኦዲተር ፍቃድ ለማግኘት ሁለት የኦዲት ቡድን ሊኖረው ይገባል የሚል ሲሆን አንድ የፐብሊክ ኦዲተር ፍቃድ ያለው የኦዲት ድርጅት ቢያንስ ሰባት የኦዲት ቡድኖችን ማሠማራት የሚችል አቅም ሊኖረው ይገባል ብለን እናምናለን፡፡ ምክንያቱም አንድ የኦዲት ቡድን በአንድ ጊዜ የኦዲት አገልግሎት መስጠት የሚችለው ለአንድ ድርጅት ነው፡፡ በሒሳብ መዝጊያ ወቅት ለብዙ ደንበኞች የኦዲት አገልግሎት የሚሰጥ በመሆኑ ሁለት የኦዲት ቡድን ያለው የኦዲት ድርጅት በግብር ወቅት በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ተጠቃሚዎችን እንዴት ሊያገለግል ይችላል? በተጨማሪም በኦዲት ቡድኑ ማኔጀር እና ከፍተኛ ባለሙያ የሥራ ልምድ ከፍ ቢደረግ እና እንደቅደም ተከተላቸው ሁለት እና ሦስት ዓመት ቢሆን የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን ቦርዱ ባከናወነው የኦዲት ሥራ ጥራት ማረጋገጫ ምርመራ የተከናወኑ የኦዲት ሥራዎች የጥራት ደረጃ አነስተኛ ሆኖ በመገኘቱ ቦርዱ የኦዲት ሙያ የአገልግሎት ጥራትን ለማስጠበቅ እንዲረዳ አንድ የፐብሊክ የኦዲት ድርጅት ሊኖረው የሚገባውን ዝቅተኛ የኦዲት ቡድን ቁጥር እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

ከዚህ ውጪ ፐብሊክ ኦዲተሮች ሊኖራቸው የሚችለው የደንበኛ ቁጥር እና የሥራ ጫና የተለያየ ስለሚሆን የሥራውን ሥፋት እና ጥልቀት በመገምገም ተጨማሪ የሰው ኃይል የመቅጠር ኃላፊነት ለባለሙያው ቢተው የተሻለ ይሆናል በሚል የተሰጠውን አስተያየት አልተቀበልነውም፡፡

32. በአንቀጽ 8(3)(በ) (በተሻሻለው መሠረት) ሥር የፐብሊክ ኦዲተር ፍቃድ ለማግኘት የ1 ሚሊዮን የመሥሪያ ካፒታል መስፈርት የተቀመጠ ሲሆን አብዛኛው የኦዲት መሥሪያ ሶፍትዌሮች ከውጪ በኪራይ መልክ የሚገዙ በመሆኑ እና በተለይም የሽርክና ማኅበር ሲሆን የሥራ ማስኬጃ (የሠራተኛ ደመወዝ፣ ጥቅማ ጥቅም፣ የቢሮ ኪራይ እና ሌሎች ወጪዎች) ወጪው ከፍተኛ በመሆኑ የመሥሪያ ካፒታሉ ወደ 10 ሚሊዮን ከፍ ቢል የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በባለሙያው ላይ ከፍተኛ ጫና የሚያስከትል በመሆኑ እና ባለሙያው የሚሰጠው አገልግሎት ሙያዊ አገልግሎት በመሆኑ አስተያየቱን አልተቀበልነውም፡፡

33. በአንቀጽ 9 ላይ የጣምራ ፍቃድ አሰጣጥን በሚመለከት ቦርዱ ሰፋ ባለ የማማከር ሥራ ላይ ለተሰማራ ኩባንያም (ኃ/የ/የግ/ማ ወይም አክሲዮን ማኅበር) የጣምራ ፍቃድ ቢሰጥ ለኩባንያው የሥራ ቅልጥፍና ይረዳል፡፡ ለምሳሌ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ኩባንያ አቋቁመው አገልግሎት ለሚሰጡ ባለሙያዎች የኢንቨስትመንት ፍቃድ ይሰጣል፡፡ የኢንቨስትመንት አማካሪነት አገልግሎት ደግሞ የፋይናንሻል ትንተና እና ለሕዝብ የሚቀርበውን ፕሮስፔክተስ ዝግጅት አገልግሎት ይሰጣል፡፡ በዚህ ወቅትም ቀደም ብሎ የተሰራው የሒሳብ ሥራ ክለሳ ሊያስፈልገው ይችላል፡፡ ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት አገልግሎት ለሚሰጡ ድርጅቶች ቦርዱ የሒሳብ ሥራ ፍቃድ ሊሰጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ሙያው ሊያድግ የሚችለው ሙያተኞች ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች እንዲካተቱበት ሲፈቀድ ነው። ይህም ሙያው በሠው ኃይል፣ በቴክኖሎጂ እና በአሰራር እንዲጠነክር እና ቢያንስ በምስራቅ አፍሪካ ተወዳዳሪ እንዲሆን የሚያስችለው ይሆናል የሚሉ አስተያየቶች የተሰጡ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 847/2006 እና በደንብ ቁጥር 332/2007 መሠረት የሒሳብ ወይም ኦዲት አገልግሎት የሚሰጠው አንድ ባለሙያ ብቻውን (sole proprietorship) በመሆን ወይም ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር የሽርክና ማኅበር (Partnership) በማቋቋም /ሁሉም ሽሪኮች የጸና የሙያ ፍቃድ ያላቸው ባለሙያዎች/ ነው፡፡ በመሆኑም ሙያዊ አገልግሎት የሚሰጡ አመልካቾች በዘርፉ የጸና የሙያ ፍቃድ ያላቸው በመሆኑ እና ከተጠቀሱት የንግድ ማኅበር ዓይነቶች ውጪ ፍቃድ

እንዲሰጥ ማድረግ ከአዋጁ እና ከደንቡ ጋር የሚጋጭ በመሆኑ እና የአዋጅ እና የደንብ ማሻሻያ የሚጠይቅ በመሆኑ አስተያየቱን አልተቀበልነውም፡፡

34. በአንቀጽ 9(1) ላይ ጣምራ ፍቃድ ማግኘት የሚፈልግ ኦዲተር ማመልከቻ ማቅረብ እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን የኦዲት ፍቃድ የተሰጠው ድርጅት የሒሳብ ሥራ እንዲሠራ መፈቀድ አለበት እንጂ ለተመሳሳይ ነገር ሁለት ጊዜ ማመልከቱ የሥራ ቢሮክራሲ ይፈጥራል፤ በተጨማሪም ጣምራ ፍቃድ ባይጠየቅ እና የጥቅም ግጭት በማይፈጥር ሁኔታ እንዲሠራ ቢፈቀድ እንዲሁም የሒሳብ ሥራ ለሰራበት ድርጅት እራሱ የኦዲት ሥራ አገልግሎት መስጠት የማይፈቀድ መሆኑ በግልጽ ቢቀመጥ የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በሥራ ላይ ያሉ ኦዲተሮች የጣምራ ፍቃድ ለማግኘት ማመልከቻ ማቅረብ የሚጠበቅባቸው ቢሆንም አዲስ አመልካች ከሆነ ግን የጣምራ ፍቃድ ለማግኘት የተዘረጋ የአሰራር ሥርዓት በመኖሩ አንድ ግዜ ብቻ በማመልከት ፍቃድ ማግኘት የሚችልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። እንዲሁም ማንኛውም ኦዲተር የሒሳብ ሥራ (የኦዲት ሥራ ያልሆነ አገልግሎት) ለሰራለት ድርጅት የኦዲት ሥራ አገልግሎት መስጠት የማይችል መሆኑ አንቀጽ 9(6) ሥር በግልጽ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

35. በአንቀጽ 10(1) እና 11(3)(ለ) ሥር የሽርክና ማኅበር በማቋቋም የሒሳብ ወይም የኦዲት አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች በቅድሚያ ከቦርዱ የተሰጠ የጸና የሙያ ፍቃድ ሊኖራቸው እንደሚገባ የተደነገገ ሲሆን በሽርክና ማኅበር ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ባለሙያዎች ወደ ሽሪክነት በቀጥታ እንዲያድጉ የሚደረግበት ሁኔታ አለ፡፡ ስለሆነም የቦርዱን ምዘና እስካሚሉ ድረስ ከሽርክና ማኅበሩ የሥራ መልቀቂያ ባይጠየቁ፤ እንዲሁም ከቦርዱ የተሰጠ የጸና የሙያ ፍቃድ እንዲያወጡ ሳይገደዱ ሊስተናገዱ የሚችሉበት ሥርዓት/ሕግ ቢዘረጋ የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን የሥራ መልቀቂያ በሚመለከት በተሰጠው አስተያየት መሠረት የሥራ መልቀቂያ ከማቅረብ ነጻ በማድረግ የሽርክና ማኅበሩ ሽሪክ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ከማኅበሩ የተሰጠ ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ በሚል የተስተካከለ ሲሆን ከቦርዱ የተሰጠ የጸና የሙያ ፍቃድ እንዲያቀርቡ አይገደዱ የሚለው አስተያየት ግን ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ምክንያቱም የሽርክና ማኅበሩን የሚቀላቀለው ባለሙያ ፍቃድ ለማግኘት የተቀመጡትን መስፈርቶች ማሟላቱ ተመዝኖ መረጋገጥ እና ለዚህም ማስረጃ መስጠት ተገቢ በመሆኑ፡፡

36. በአንቀጽ 11(3)(መ) ሥር በቦርዱ ተቀባይነት ያለው የድርጅት ሥም በሚመለከት የተደነገገ ሲሆን በቦርዱ ተቀባይነት ያለው የድርጅት ሥም ሲባል መስፈርቱ ምንድነው፣

ማብራሪያ ይፈልጋል፣ ከንግድ ሕጉ ጋር መገናዘብ አለበት የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 847/2006 አንቀጽ 21 ሥር ተቀባይነት ያለው የድርጅት ሥም የሚመዘንበት መስፈርት በግልጽ የተዘረዘረ በመሆኑ በዚህ መመሪያ ላይ በድጋሚ ማስቀመጥ ተገቢ ስለማይሆን አስተያየቱን አልተቀበልነውም፡፡

37. በአንቀጽ 11(3)(ረ) ሥር የሽርክና ማኅበር በመቋቋም የኦዲት አገልግሎት ለመስጠት የኦዲት ቡድን ማደራጀት እንደ መስፈርት ተቀምጧል ነገር ግን የሽርክና ማኅበሩ ሳይመሰረት ሠራተኛ እንዴት ሊቀጥር ይችላል፣ እንዲሁም ከፍተኛ ወጪ ስለሚጠይቅ በሽርክና መሥራትን አያበረታታም የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በረቂቁ አንቀጽ 11(6) ሥር ባለሙያው የኦዲት ቡድን እንዲያቋቁም የሚገደደው ከቦርዱ ፍቃድ ከወሰደ ከሁለት ወራት በኋላ በመሆኑ እና ቦርዱ ባከናወነው የኦዲት ሥራ ጥራት ማረጋገጫ ምርመራ መሠረት የሽርክና ማኅበሩ ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት ለመስጠት እንዲችል ቢያንስ ሁለት የኦዲት ቡድን ሊኖረው እንደሚገባ የታመነ ስለሆነ የተሰጠው አስተያየት ተቀባይነት የለውም፡፡

38. በአንቀጽ 12 ሥር የውጭ አገር ዜግነት ያለው ባለሙያ/ድርጅት የሙያ ፍቃድ ስለሚያገኝበት ሁኔታ የተደነገገ ሲሆን ትውልደ ኢትዮጵያን የሆኑ ሰዎች ቢያካትት የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በተሰጠው አስተያየት መሰረት በረቂቁ ላይ ትውልደ ኢትዮጵያውንን የሚመለከት ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

39. በአንቀጽ 14 ሥር የውጭ አገር ዜግነት ያለው ድርጅት የሙያ ፍቃድ ስለሚያገኝበት ሁኔታ ተደንግጓል ይሁን እንጂ በየትኛውም አገር የሙያ ብቃት ማረጋገጫ/ፍቃድ የሚሰጠው ለግለሰብ ሲሆን ግለሰቡ ፍቃድ ካገኘ በኋላ የሌላን ድርጅት የንግድ አርማ ሊጠቀም ወይም የድርጅቱ ሽሪክ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም ድንጋጌው መቃኘት ያለበት የሙያ ፍቃዱ ለግለሰብ ተሰጥቶ ግለሰቡ የሚሰራበትን ድርጅት ሥም በቦርዱ እንዲያስመዘግብ በሚፈቅድ መልኩ ሊሆን ይገባል የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በተሰጠው አስተያየት መሰረት በረቂቁ ላይ ማስተካከያ ተደርጓል፡፡

40. በአንቀጽ 16 ሥር ከቦርዱ ፍቃድ ተሰጠው ባለሙያ ቅርንጫፍ መ/ቤት ለመክፈት በቅድሚያ ቦርዱን ማሳወቅ እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን ድንጋጌው ለአተገባበር ስለሚያስቸግር ባለሙያው ቅርንጫፍ መ/ቤት ከከፈተ በኋላ ለቦርዱ ቢያሳውቅ ይሻላል የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን ቦርዱ በባለሙያዎች ላይ የክትትል፣ ድጋፍ እና ቁጥጥር ሥራ የሚያከናውን በመሆኑ እና የባለሙያዎችን መረጃ በወቅቱ የመያዝ እና የማደራጀት

ሥራ ስለሚያከናውን እንዲሁም ከባለሙያዎች መረጃ ጋር በተያያዘ በሦስተኛ ወገኖች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወቅታዊ መረጃ ለመስጠት እንዲያስችል ታስቦ የተቀረጸ ድንጋጌ ስለሆነ የተሰጠው አስተያየት ተቀባይነት አላገኘም፡፡

41. በአንቀጽ 16(4) ሥር ቅርንጫፍ መ/ቤት የሚከፍት ባለሙያ ቅርንጫፍ በሚከፍትበት ሥፍራ ንግድ ፍቃድ እንዲያወጣ የሚገደድ ከሆነ ቅጂውን ለቦርዱ ማቅረብ እንዳለበት የሚደነግግ ሲሆን ይደነግጋል አሁን ባለው የንግድ አሰራር ባለሙያው ቅርንጫፍ ሲከፍት ማሳወቅ እና ምዝገባ ማከናወን እንጂ ንግድ ፍቃድ አያወጣም ስለሆነም ጫና ስለሚፈጥር እንደገና ቢታይ የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን ባለሙያው የንግድ ፍቃድ ቅጂ እንዲያቀርብ የሚገደደው ቅርንጫፍ በሚከፍትበት ሥፍራ ንግድ ፍቃድ እንዲያወጣ የሚያስገድድ አሰራር ካለ ወይም ልዩ ምዝገባ በማድረጉ የሚሰጠው የምሥክር ወረቀት ሲኖር ብቻ በመሆኑ አስተያየቱ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

42. በአንቀጽ 24(7) ሥር አንድ ባለሙያ የሙያ ፍቃዱን ለማሳደስ የደንበኞችን ዝርዝር እና ለአገልግሎቱ የተቀበለው የክፍያ መጠን የያዘ ሰነድ ማቅረብ እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን ባለሙያው ለአገልግሎቱ የተቀበለውን ክፍያ እንዲገልጽ ማድረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ ምክንያቱም መረጃው የባለሙያው የግል መረጃ በመሆኑ እና ቦርዱ ከተቋቋመለት ዓላማ አንጻር ተዛማጅነት የሌለው በመሆኑ እንዲሁም ቦርዱ መረጃውን በሚፈልግ ጊዜ በምርመራ ወቅት ሊያገኘው የሚችል ነው የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን ቦርዱ ፍቃድ በሰጣቸው ባለሙያዎች ላይ የሥራ ጥራት ማረጋገጫ ምርመራ ለማከናወን ድርጅቶችን ለመምረጥ/ለመለየት ከሚጠቀመው መስፈርቶች መካከል አንዱ ድርጅቱ ከደንበኛው የተቀበለው የአገልግሎት ክፍያ መጠን ነው፤ ይህ አሠራር በዓለም አቀፍ የሥራ ጥራት ማረጋገጫ ደረጃዎች የሚደገፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚተገበር አካሄድ በመሆኑ አስተያየቱን አልተቀበልነውም፡፡

43. በአንቀጽ 25 ሥር የፍቃድ ዕድሳት በሚደረግበት የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳደስ ያልቻለ ባለሙያ ለዘገየበት እያንዳንዱ ቀን ቅጣት በመክፈል ሊያሳድስ እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን ቅጣቱ በየቀኑ ከሚሰላ ይልቅ በየወሩ ቢደረግ፣ እንዲሁም ቅጣቱ የበዛ ስለሚመስል በወር እስከ 2000 ብር ይቀጣል በሚል ቢስተካከል የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን ለአንድ ቀን የዘገየ እና 29 ቀን የዘገየን አመልካች ተመሳሳይ ቅጣት መቅጣት ፍትሐዊ ስለማይሆን፤ እንዲሁም ቀድሞ በነበረው መመሪያ ላይ የተቀመጠው የቅጣት መጠን ላይ

ማስተካከያ የተደረገው የወቅቱን የዋጋ ግሽበት መጠን በመስላት በመሆኑ የተሰጠውን አስተያየት አልተቀበልነውም፡፡

44. በአንቀጽ 28 ሥር በማስረጃ ተደግፎ መቅረብ ያለበት የ20 ሰዓት የሙያ ማጎልበቻ ሥልጠና ቦርዱ በእራሱ ወይም ከሌሎች ጋር በመተባበር የሰጠው ሥልጠና መሆን እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን ድንጋጌው ከዓለም አቀፍ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ጋር ይጣረሳል፡፡ ምንም እንኳን ቦርዱ የሚሰጠውን ሥልጠና ጠቃሚ ቢሆንም በሌሎች ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የሚሰጡ ሥልጠናዎች ተቀባይነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የሙያ ሥልጠና ዓላማው ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠት ራስን ማጎልበት የግድ ስለሆነ ነው፡፡ ስለሆነም እንደ ACCA ዓይነት ድርጅቶች፣ የውጪ የትምህርት ፕሮግራሞች፣ ኦንላይን ኮርሶች፣ ብሔራዊ ባንክ፣ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን እና ገቢዎች የሚሰጠው ሥልጠና በማስረጃ እስከተደገፉ ድረስ በቦርዱ ተመዝነው ተቀባይነት እንዲኖራቸው ቢደረግ የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በሌሎች ተቋማት የሚሰጡ ሥልጠናዎች በቦርዱ ተመዝነው ተቀባይነት የሚያገኙበት ሁኔታን የሚፈቅድ ድንጋጌ በረቂቁ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

45. በአንቀጽ 30(2) (ለ፣ ሐ እና መ) ሥር ከግል ድርጅት ወደ ሽርክና ማኅበር የአደረጃጀት ለውጥ ስለሚደረግበት ሁኔታ የተደነገገ ሲሆን የተቀመጠው መስፈርት ባለሙያው እየሰራ የሚተዳደርበትን ድርጅት ዘግቶ ሂደቶቹን እንዲያሟላ የሚያስገድድ ነው፤ የመስፈርቶቹ አፈጻጸም በባሕሪያቸው ረዘም ያለጊዜ የሚወስድ ነው በተለይ ከግብር ሰብሳቢው ተቋም የሚሰጠውን ማስረጃ ለማቅረብ፤ ስለሆነም በሥራ ላይ እያሉ ጎን ለጎን መፈጸም የሚቻልበት ሁኔታ ቢመቻች የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን አንቀጽ 30(2) (ለ) በሚመለከት የሚቀርበው የጽሁፍ ማረጋገጫ በእራሱ በባለሙያው ተሞልቶ የሚቀርብ በመሆኑ ጊዜ የሚወስድ አይሆንም፡፡ አንቀጽ 29(2) (ሐ) በሚመለከት የሚቀርበው ማስረጃ ድርጅታቸውን ለመዝጋት ማመልከቻ እስካቀረቡበት ድረስ ያለባቸውን የበሰለ ግብር መክፈላቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንጂ ድርጅቱን ለመዝጋት በገቢዎች ሚ/ር ኦዲት ከተደረገ በኋላ የሚሰጠውን ክሊራንስ አለመሆኑን፤ እንዲሁም 29(2) (መ) በሚመለከት በመርህ ደረጃ ሁለት ፍቃድ በአንድ ጊዜ ይዞ አገልግሎት መስጠት የማይፈቀድ በመሆኑ አስተያየቱን አልተቀበልነውም፡፡ ነገር ግን ድንጋጌው ግልጽ እንዲሆን ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

46. በአንቀጽ 33(3)(ሠ) ሥር አንድ የሽርክና ማኅበር ሽሪኮቹ በመውጣታቸው ምክንያት አንድ ሽሪክ ብቻ የሚቀረው ከሆነ በንግድ ሕጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተጨማሪ ሽሪክ መጨመር ካልቻለ ፍቃዱ እንደሚሰረዝ የተደነገገ ሲሆን ባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር በንግድ ሕጉ ስለሚፈቀድ ድርጅቱን መዝጋቱ አግባብነት የለውም የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 847/2006 መሠረት የሂሳብ ወይም የኦዲት አገልግሎት መስጠት የሚችለው በግሉ ወይም የሽርክና ማኅበር በመቋቋም ብቻ ነው፡፡ ባለ አንድ አባልም ሆነ ከአንድ አባል በላይ ያለው ኃ/የተ/የግ/ማኅበር በማቋቋም የሒሳብ ወይም የኦዲት አገልግሎት መስጠት የተፈቀደ አይደለም፡፡ ስለሆነም ተፈጻሚነት የሚኖረው ድንጋጌ በንግድ ሕጉ ላይ ያሉት የሽርክና ማኅበርን እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበርን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ብቻ በመሆናቸው የተሰጠውን አስተያየት አልተቀበልነውም፡፡

47. የሽርክና ማኅበር ሲቋቋም ሌሎች ድርጅቶች የሽርክና ማኅበሩ ሽሪክ መሆን የሚችሉበት ሥርዓት ቢፈቀድ የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በአዲሱ የንግድ ሕግ መሠረት ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር ሽሪኮች ሊሆኑ የሚችሉት አግባብ ካለው አካል የሙያ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ የተሰጣቸው ባለሙያዎች ወይም ከማኅበሩ ጋር ተመሳሳይ ወይም ተያያዥ የሆነ አገልግሎት የሚሰጡ ኃላፊነታቸው የተወሰነ የሽርክና ማኅበራት ናቸው በሚል የተደነገገ በመሆኑ ይህን መስፈርት በማሟላት አገልግሎት መስጠት የሚቻልበት ሥርዓት በመኖሩ በዚሁ አግባብ ጥያቄው ከቀረበ የሚስተናገዱበት ሁኔታ ያለ በመሆኑ አስተያየቱን አልተቀበልነውም፡፡

48. በአንቀጽ 35(1) ሥር ማንኛውም ባለሙያ ከሽርክና ማኅበር በመውጣት በግሉ አገልግሎት ለመስጠት የሚያቀርበው ማመልከቻ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን ስድስት ወራት የሚለው ጊዜ አጭር ስለሆነ ወደ 1 ዓመት ከፍ ቢል የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን ከሽርክና ማኅበር የሚወጣ ባለሙያ በግሉ አገልግሎት ለመስጠት ማሟላት የሚጠበቅበት ቢሮ መከራየት፣ ንግድ ፍቃድ ማውጣት እና የሙያ መድን ዋስትና ማስረጃ ማቅረብ ነው፤ ይህን ለማሟላት የተቀመጠው የስድስት ወራት ጊዜ በቂ ነው፤ አዲስ የሙያ ፍቃድ የሚያወጣ አመልካች ተመሳሳይ የሆኑ መስፈርቶችን የሚያሟላው በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ነው፤ የስድስት ወራት ጊዜ የተሰጠው በሥራ ላይ የነበሩ ባለሙያዎች በመሆናቸው ከደንበኞቻቸው ጋር ያላቸውን

ግንኙነት መስመር እንዲያሲዙ ወይም መቋጨት እንዲችሉ ታሳቢ በማድረግ ስለሆነ የቀረበው አስተያየት ተቀባይነት የለውም፡፡

49. በአንቀጽ 37(13) እና (14) ላይ ባለሙያው የደንበኞችን እና የሠራተኞችን መረጃ በአግባቡ አደራጅቶ መያዝ እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን በአግባቡ የሚለው ቃል አሻሚነት ስላለው በግልጽ ቢቀመጥ የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን አግባቡ የሚለው ቃል ከድንጋጌው ውስጥ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

50. በአንቀጽ 37(19) ሥር የሙያ አገልግሎት ከመሰጠቱ በፊት ከደንበኛው ጋር የጽሁፍ ውል መያዝ እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን ተደንግጓል ከሰኔ እስከ ጥቅምት ባለው ጊዜ የሚመጡ ሰነዶች በጉዳይ አስፈጻሚ ጭምር የሚመጡ ስለሆነ ከጊዜው መጨናነቅ አንጻር ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ችግር አለው የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን ባለሙያው አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት ደንበኛውን በአግባቡ የማወቅ እና ውል የመፈጸም ግዴታ አለበት፤ ይህ ካልሆነ ባለሙያው እራሱ ባላዘጋጀው የሒሳብ መግለጫ ወይም ሪፖርት ማኅተም እና ፊርማ እንዲያሳርፍ በር የሚከፍት በመሆኑ የቀረበው አስተያየት ተቀባይነት አላገኘም፡፡

51. በአንቀጽ 44 ሥር ለአገር ውስጥ የሒሳብ ሙያ ማኅበር የተቀመጠው መስፈርት የሒሳብ ሙያ ማኅበሩ ዓለም አቀፍ የሒሣብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን ሙሉ አባል የሆነ ወይም አባል ለመሆን የሚያስችለውን ፕሮግራም ቀርፆ የሚንቀሳቀስ ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን የሒሳብ ሙያ ማኅበራት አክሪዲቴሽን የሚያገኙበትን መስፈርት በዝርዝር ማስቀመጥ ይገባል እንጂ ዓለም አቀፍ የሒሣብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን ሙሉ አባል የሆነ ወይም ለመሆን የሚያስችለውን ፕሮግራም ቀርፆ የሚንቀሳቀስ ስለመሆኑ ማስረጃ እንዲቀርብ መጠየቁ አግባብነት የለውም የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን የሒሳብ ሙያ ማኅበሩ የሚያፈራቸው ባለሙያዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እና ዕውቅና እንዲኖራቸው ለማድረግ የግድ ማኅበሩ የዓለም አቀፍ ሒሳብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን አባል ወይም አባል ለመሆን የሚያስችለውን ፕሮግራም ቀርፆ የሚንቀሳቀስ ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ የሚጠበቅበት በመሆን አስተያየቱ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

52. በአንቀጽ 50(1) ሥር ለሕዝብ ጥቅም ላለባቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት ኦዲት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ የተመሠከረለት ኦዲተር በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የፐብሊክ ኦዲተር ፍቃድ ካልያዘ አገልግሎት እየሰጠ መቀጠል አይችልም በሚል

የተደነገገ ሲሆን የተቀመጠው ጊዜ አጭር ነው፤ በተለይ የኦዲት ድርጅቶቹ ቀድመው የውል ግዴታ የገቡበት ሥራ ሊኖር ስለሚችል የጀመሩትን ሥራ እስኪያጠናቅቁ፣ በአግባቡ ለሌላ ባለሙያ እስኪያስተላልፉ ወይም ደንበኞቻቸው ሌላ አማራጭ መውሰድ የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ ሊሰጥ ይገባል የሚል አስተያየት የቀረበ ሲሆን የፐብሊክ ኦዲተር ፍቃድ ለማግኘት የሚያመለክቱ ሰዎች የተመሠከረለት የኦዲት ፍቃድ ያላቸው ባለሙያዎች በመሆናቸው እና ጥቂት መስፈርቶችን ብቻ እንዲያሟሉ የሚጠየቁ በመሆኑ የተቀመጡትን መስፈርቶች ለማሟላት የተቀመጠው ጊዜ ከበቂ በላይ ስለሆነ አስተያየቱን አልተቀበልነውም፡፡

53. በአንቀጽ 50(2) ሥር መመሪያው ከመውጣቱ በፊት ከቦርዱ የኦዲት ፍቃድ የተሰጠው ባለሙያ ወይም ድርጅት መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባለው የስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ እንደ አግባብነቱ የሙያ መድን ዋስትና እና የኦዲት ቡድን የማቋቋም ግዴታ ማሟላት እንዳለበት በሚል የተደነገገ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 847/2006 አንቀጽ 54(3) መሠረት በአዋጁ የተቀመጡትን መስፈርቶች ያላሟላ ባለሙያ በስድስት ዓመት ውስጥ ሥራውን እየሰራ ማሟላት እንደሚችል፤ እንዲሁም ኢንስቲትዩት ባልተቋቋመበት ሁኔታ እና በውጭ አገር ለመማር የሚወስደውን ግዜ ታሳቢ ካለማድረጉ በተጨማሪ የባለሙያውን የመሥራት መብት የሚጋፋ በመሆኑ ማስተካከያ ቢደረግበት የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን የሽግግር ድንጋጌው በሥራ ላይ ያለውን ባለሙያ የተመሠከረለት የሒሳብ ባለሙያ (CPA) እንዲሆን የሚያስገድድ ሳይሆን በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተመሠከረለት ኦዲተሩ በተሻሻለው መጠን መሠረት የሙያ መድን ሽፋን እንዲገባ እና የኦዲት ቡድን እንዲያቋቁም የሚጠይቅ ሲሆን የሒሳብ ባለሙያው ደግሞ በተሻሻለው መጠን መሠረት የሙያ መድን ሽፋን እንዲያቀርብ የሚጠይቅ በመሆኑ እነዚህን መስፈርቶች አሚልቶ መቅረብ ለባለሙያው ፈታኝ ባለመሆኑ የቀረበውን አስተያየት አልተቀበልነውም፡፡